መላኢካ “ሶላት ከእንቅልፍ ይበልጣል (አሶላቱ ኸይሩን ሚነን-ነውም)” ሲል ወደ ጀነት ጠራህ። አንተ ግን “ሌሊቱ ረጅም ነው። መተኛትህን ቀጥል!” የሚለውን የሸይጧን ውትወታ ተቀበልክ።

### 4) ድብርትና ስንፍና ይሰፍርበታል

የፈጅር ሶላት ሳይሰግድ በእንቅልፍ የሚያነጋ ሰው በባህሪው ድብርትን አሳዶ እንደሚመጥ ስፖንጅ ነው። በአቋሙ እንደ መስታወት ነው። ተዓምራት ሲያጋጥመው አንፀባርቆ ብቻ ይመልሳል እንጂ እርሱ ዘንድ የሚያስቀረው አንዳች ነገር የለም። በስሜቱ እንደ ድንጋይ ነው። በተግሳፅ አለንጋ ቢገረፍም ምንም ዓይነት ህመም አይሰማውም።

ከዚህ በተጨማሪ አላህን ከመገዛት መሳነፍ እንደ ብረት ሲሆን ግለሰቡ እንደ ማግኔት ነው። ወደ እሱ እየሳበ ይለጥፈዋል። በተከታታይ ድብርትና ስንፍና ውስጥ ይዋልላል። ምንዳ የምታስገኝ የጣት እንጓን ያክል ሥራ ከስንፈቱ የተነሳ የተራራ ያክል ገዝፋ ትታያለች። ለዚህ ነው ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) አንድ ሰው በሚተኛበት ጊዜ ሸይጣን ማጅራቱ ላይ ሶስት ትብታቦችን እንደሚቋጥርና እነኚህ ትብታቦች የሚፈቱት ከእንቅልፍ በመንቃት፣ ዉዱእ በማድረግና ሶላት በመስገድ ብቻ መሆኑን የገለፁት። አለበለዚያ ግን ይላሉ ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ)፦

((وإلا أصبح خبيث النفس كسلان))

“አለበለዚያ ግን መንፈሱ የቆሸሸና ድብርታም ሆኖ ይውላል።”[1]

ይህ ብቻም አይደለም። ነውሩ በአደባባይ ይወጣል፤ የፈፀመው ወንጀል ይጋለጣል። የክብርና የሞገስ አርማ ከርሱ ይነሳል። በምትኩ የውርደትና የመንናቅ አርማ ራሱ ላይ ይሰቀላል። ይህንን አስመልክተው አቡልሙዕተር የተሰኙ ታላቅ ዓሊም እንዲህ ይላሉ፦ “አንድ ሰው ወንጀል ሲፈፅም ሰዎች ዘንድ የተዋረደ ይሆናል።”

---

1 ቡኻሪና ሙስሊም

## 5) ጀሀነም ውስጥ ለመደፋት ምክኒያት ይሆናል

ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

((من صلى الصبح فهو في ذمة الله فانظر يابن آدم، لا يطلبنك من ذمته بشيء، فإن من يطلبه من ذمته بشيء يدركه، ثم يكبه على وجهه في نار جهنم))

‹የሱብሒን ሶላት የሰገደ በአላህ ጥበቃ ሥር ነው። የአደም ልጅ ሆይ አስተውል። አላህ ጥበቃ በሰጠው ነገር እንዳይፈልግህ። አላህ ጥበቃ በሰጠው ነገር የፈለገውን ሰው ይይዘዋል። ከዚያም በጀሀነም እሳት ውስጥ በፊቱ ይደፋዋል።›

የሱብሒ ሶላት ማንም ሊደፍረው የማይችል የአላህ ዋስትና ነው። ይህችን ሶላት ያልሰገደ አልያም የዘገየ ሰው ይህንን ዋስትና እንዳስደፈረ ይቆጠራል። የታላቁ ጌታ ቁጣም በእርሱ ላይ ይሆናል፤ ቅጣቱም በዱንያ እንቅልፍ ውስጥ የተደፋ ፊቱ በአኼራ እሳት ውስጥ መደፋት ይሆናል። አላህ (ሱ.ወ) ይህንን ባርያ በዚህ ቅጣት ሲቀጣው ፈፅሞ አልበደለውም፤ በራሱ ላይ በፈፀመው በደል ምክንያት የተበየነበት ቅጣት ነውና።

## 6) የራስ ቅል የመፈጥፈጥ አደጋን ያስከትላል

ቡኻሪ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተረጋገጠ ዜና ይነግሩናል። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በህልም ያዩትን ክስተት እንዲህ ይገልጻሉ። ‹በማጅራቱ ተንጋሎ የተኛ ሰው አየሁ። ሌላኛው ሰው ደግሞ እላዩ ላይ ቆሞ የተኛውን ሰው ራስ በድንጋይ ይወግረዋል። ድንጋዩ የሰውዬውን የራስ ቅል ይፈጠፍጥና ይንከባለላል። የሚወግረው ሰው ድንጋዩን ለማምጣት ሲንቀሳቀስ የተፈጠፈጠው ሰው የራስ ቅልም ወደነበረበት ይመለሳል። ከዚያም መጀመሪያ እንደወገረው በድጋሚ ይወግረዋል። ጂብሪልና ሚካኢል ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያዩትን ግለሰብ ማንነት ሲያብራሩ፡- "ቁርኣንን የሚያውቅ ነገርግን የማይሰራበት እና ግዴታ ሶላትን በእንቅልፍ የሚያሳልፍ ሰው ነው።› ነበር ያሉት።



CamScanner

ኢብኑ አል-ዐረቢ የሚባሉ ታላቅ ዓሊም፡- “ግዴታ ሶላትን በመኝታ የሚያሳልፍ ሰው የሚቀጣው ቅጣት የራስ ቅሉ ላይ የመሆኑ ምክንያት የእንቅልፍ ማዕከሉ ጭንቅላት በመሆኑ ነው፡፡” ብለዋል፡፡ (ፈትሑልባሪ)

### *7) ሲሳይ ያስከለክላል*

ኢብኑል ቀይም አልጀውዚ “ዛዱል መዓድ” በተሰኘ እውቅ መፅሃፋቸው ውስጥ እንዲህ ይላሉ፡፡ “የንጋት እንቅልፍ ሲሳይ (ሪዝቅ) ያስከለክላል፡፡ ምክኒያቱም የንጋት ሰዓት ሪዝቅ የሚከፋፈልበት ጊዜ ነውና፡፡ ያለ ምክንያት የሚተኛ ሰው ራሱን ከሲሳይ እንደከለከለ ይቆጠራል፡፡ በአንድ ወቅት ዐብደላህ ኢብኑ ዐባስ (ረ.ዐ) ልጃቸው ከሱብሒ በኋላ ተኝቶ በማየታቸው “ተነስ! ሲሳይ በሚከፋፈልበት ሰዓት ትተኛለህ እንዴ?” ሲሉ ገስፀውታል፡፡



CamScanner

## 1) ምሽት መቆየቱን ተውና ቀደም ብለህ ተኛ

አቢ. በርዛህ ባስተላለፉት ሐዲስ ‹የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የዒሻእ ሶላትን የተወሰነ ሰዓት ያዘገዩ ነበር:: ከዒሻእ ሶላት በፊት መተኛት እና ከዒሻእ በኋላም ወሬ አይወዱም ነበር› ብሏል::

ኢማም አልነወዊይ ከዒሻእ ሶላት በኋላ ማውጋት የማይጠላባቸውን ሁኔታዎች በሶሒሕ ሙስሊም ማብራሪያቸው ላይ እንዲህ ዘርዝረዋል:-

“ከዒሻእ ሶላት በኋላ ማውጋትና ወሬ መያዝ የተጠላበት ምክንያት ረጅም ሰዓት ማምሸተን ሊያስከትል ስለሚችል ነው:: የሌሊት ሶላትንና የፈጅር ሶላትን በሚገባው ጊዜ ከመስገድ ይልቅ በእንቅልፍ መሸነፍን እንዳያስከትል ያሰጋል::

የሚጠላው የወግ ዓይነት ደግሞ አልባሌና ምንም ዓይነት ፋይዳ የሌለው ሲሆን ነው:: መልካምና ጠቀሜታ ያለው ከሆነ የሚጠላ አይሆንም:: ለምሳሌ:- ትምህርት ማጥናት፣ ከደጋግ ሰዎች ዘንድ ምክር ማድመጥ፣ እንግዳን ማዋራት፣ ሙሽራን ማስደሰት፣ ከሚስትና ልጆቹ ጋር መጨዋወት፣ የመንገደኞችን ንብረት መሰብሰብና ማስተባበር፣ በሰዎች መካከል ማስታረቅ፣ በሽምግልና ተግባር ላይ መሰማራት፣ በመልካም ማዘዝ፣ ከመጥፎ መከልከል፣ ጠቀሜታ ወዳለው ነገር መምራት፣... እና የመሳሰሉት ከዒሻእ ሶላት በኋላ ቢከናወኑ የሚጠሉ ተግባሮች አይደሉም::

ዑመር ኢብኑልኸጣብ (ረ.ዐ.) ከዒሻእ ሶላት በኋላ ሲያወሩና ሲጫወቱ የሚያዩዋቸውን ሠዎች በልብሳቸው ጫፍ ገረፍ ገረፍ እያደረጉ እንዲህ ይሏቸው ነበር:- “የሌሊቱን መጀመሪያ በጨዋታ መጨረሻውን በእንቅልፍ ለማሳለፍ ነውን?!”

## 2) የመኝታ ሥነ-ሥርዓት ጠብቅ

ከመተኛትህ በፊት ውዱእ አድርግ:: ከዚያም የዉዱእ ሁለት ረከዐህ ሶላት ስገድ:: የመኝታ ውዳሴዎችን አትዘንጋ:: በቀኝ ጎንህ በኩል ተኛ:: የቀኝ እጅህን መዳፍ ፊትህ ሥር አድርግ:: ሙዐወዘተይንን (የአል-ፈለቅ እና የአን-ናስ ምዕራፎች) ሁለት መዳፎችህ ላይ አንብበህ ከሰውነት ክፍልህ –ከብልቶችህና ከእግርህ ሥር ውጭ– የቻልከውን ያህል አብስበት:: ሌሎች የመኝታ ዚክሮችንም አድርስ::

## 3) መልካም ዝራ መልካምን ታጭዳለህ

መልካም ስራ ከሰራ በኋላ ወደ ፍራሹ የሄደ ሰው የፈጅር ሶላትን ለመስገድ የተገባ ሰው ይሆናል:: ምክንያቱ ወዲህ ነው:: የትኛዋም መልካም ስራ ብቻዋን መሆን አትሻም:: ሌላ መልካም ስራ ትጠራና ትጎዳኛታለች ስለሆነም ከመኝታህ በፊት ዝምድናን መቀጠል፣ ለወላጆችህ አስደሳች ነገር መፈፀም፣ ለጎረቤትህ በጎ መዋል፣ የሚስጥር ሶደቃ፣ በመልካም ማዘዝ፣ ከክፉ መከልከል፣ መንገድ የጠፋውን ማመላከት፣ የቲምን (ወላጅ አልባን) መንከባከብ፣ ባለጉዳይን መርዳት፣... የመሳሰሉ መልካም ተግባሮችን ፈፅም:: እነኚህ መልካም ስራዎች ፈጅር ሶላትን መስገድ የሚያስችሉ መንደርደሪያዎችና ደወሎች ይሆኑልሃል::

## 4) ከመጥፎ ነገር ራስህን አርቅ፤ ሰላም ታገኛለህ

ይህ የሚሆነው አካልህን ሐላል (ፍቁድ) ካልሆኑ ነገሮች በመቆጠብ ነው:: ከሐራም እይታ አይንህን አቅብ:: ምላስህን፣ ጆሮህንና ሌሎች አካሎችህንም ከሀራም ተግባር አርቅ::

ሐሰን አልበስሪ በአንድ ወቅት "ለምን ይሆን የሌሊት ሶላትን መስገድ የማንችለው?" ተብለው ተጠየቁ:: "ወንጀሎቻችሁ ጠፍረው ስላሰሯችሁ ነው::" በማለት መለሱ:: የተለያዩ ወንጀሎችን ፈፅሞ ወደ ፍራሹ ያመራ ሰው ቅጣት የፈጅር ሶላትን መከልከል ነው:: ወንጀሎቹ ሀሜት፣ ፋይዳ በሌለው ጉዳይ ጊዜ ማጥፋት፣ የሐራም እይታ፣ ድሃን

መናቅ፣ ቃልን ማፍረስ፣ ሐራም መብላት፣ አደራን ማጥፋት፣... እና ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ። በሌሊት ሰዓታት ክፉ የሰራ በቀን ሰዓታት እንደሚቀጣ ሁሉ በተመሣሣይ በቀን ሰዓታት ክፉ የሰራ ደግሞ በሌሊት ሰዓታት ይቀጣል። ቅጣቱም ከመልካም ሥራ መከከልከል ነው። ወንድሜ ሆይ! ይህ በርግጥም ትልቅ ቅጣት መሆኑን ልብ ይሏል።

## 5) የእኩለ-ቀን ረፍት አድርግ

አቡ ዘር አልጊፋሪይ (ረ.ዐ) ከህጻናት ድምፅ ራቅ ይሉና እኩለ-ቀን ላይ ለአጭር ሰአት ይተኛሉ። ረፍት ያደርጋሉ። ስለዚህ ተግባራቸው ሲጠየቁ እንዲህ ሲሉ መልሰዋል፦ "ነፍሴ የምጋልባት ፈረሴ ነች። በእዝነት ካልያዝኳዋት የምፈልገው ቦታ ልታደርሰኝ አትችልም።"

ይህችን ሰዓት ረፍት ማድረግ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱና በመሆኑ ነበር አቡ ዘር የሚተገብሩት። ታላቁ መሪ ያስተማሩት እንዲያ ነውና። የእኩለ-ቀን ረፍት በርግጠኝነት አካልን ዘና አድርጎ ከተቻለ ከጎህ መቅደድ በፊት አሊያም ለፈጅር ሰላት መንቃት ያስችላል።

## 6) በመልካም ሥራ አጋዥ ወንድሞችን ተጠቀም

እነኚህ ወንድሞች በኢብሊስ የሚመራውን የእንቅልፍ መልእክተኛና የስንፍና ሰራዊት ለመጋፈጥ አጋዥ ሀይል ናቸው። ያስታውሱህ ዘንድ አደራ በላቸው፤ ይቀሰቅሱህ ዘንድ አሳስባቸው። ለዚህ እንዲረዳህ እነርሱ ያሉበት አካባቢ አትጥፋ። ለአርባ ተከታታይ ቀናት ከደጋግ ሰዎች ውሎህን ካደረግክ ባህሪያቸውን ትወርሳለህ። የታመመው ልብህ ይፈወሳል። የሞተ ስብዕናህ ህያው ይሆናል።

አስታውስ፦ አላህ (ሱ.ወ.) የዋሻውን ወጣቶች ከሦስት መቶ ዘጠኝ ዓመታት በኋላ ሲቀስቅሳቸው ውሻቸውን አብሮ ቀስቅሷል፤ ተጎዳኝቷቸዋልና። ነቢዩላህ ዐዚይርን (ዐ.ሰ.) ከመቶ ዓመታት በኋላ ህያው ያደረጋቸው አብሮአቸው ከነበረው አህያቸው ጋር ነበር።

## 7) የመጭውን ዓለም ክብደት ተረዳ

‹ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ላይ የሆነ ቦታ መምጣት ከቻልክ አስር ሺህ ብር ይሰጥሃል ብትባል ምን ታደርጋለህ? በእርግጠኝነት እንቅልፍ በዐይንህ አይዞርም:: እረፍት አያስደስትህም:: በጉጉት ዓለም ስትገላበጥ ታመሻለህ:: ሰዓቱ እንዳያልፍ ካለህ ፍርሃት የተነሳ ሰላም ታጣለህ:: እያንዳንዷን ሠዓት ትቆጥራለህ:: ደቂቃዎችና ሠኮንዶችን ትከታተላለህ:: ቀጠሮው የዓመት ያህል ይርቅብሃል:: ከቀጠሮው ጊዜ በአንድ ሰዓት ቀድመህ በመገኘት ገንዘቡን የሚሠጥህን ግለሰብ ትጠባበቃለህ::

ወንድሜ ሆይ! አስር ሺህ ብር ወይስ ጀነት? የዱንያ ምንዳ ወይስ የአኼራ? የትኛው ልቦናህ ውስጥ ከበደ?! የደቂቃዎች ደስታን ከዘለዓለማዊ ፀጋና ድሎት ታስቀድማለህን?! የአኼራን ልክ በውሉ ብትረዳ ኖሮ በዱንያ ፍቅር የሰከረው ልቦናህ ከስካሩ ባንሠራራ ነበር:: ገና በልጅነት እድሜ ላይ እያለህ የሂሳብ መምህርህ ያስተማረህን አስታውስ:: ያለህበትን ሁኔታ ለመቀየር ይረዳሃልና:: ማንኛውም ቁጥር ለወሰን የለሽ ቁጥር ሲካፈል ውጤቱ ዜሮ ነው:: ዱንያ ምንም ያህል ብትገዝፍ ዘላለማዊ ከሆነው አኼራ ጋር ስትነፃፀር ምንም ነች:: ዜሮ ነች:: ምክንያቱም የዱንያ ታላቅና ግዙፍ መሆን መጨረሻው መጥፋት ሲሆን የአኼራ ደግሞ መጨረሻው ዘላለማዊነት ነው:: ለዚህ ነው ዱንያ ከአኼራ አንፃር ዜሮ የምትሆነው:: ዱንያ የማይጨበጥ ስርብዶምና አታላይ ብዥታ ነች:: እናም ዘላለማዊው አገርህ ይመችህ ዘንድ የመጨረሻ አቅምህን ተጠቅመህ ትጋ::

## 8) ጠላትህን ተበቀለው

የሱብሒ ሶላት ካመለጠህ ሸይጧንን ሊያሳምም በሚችል ቅጣት ተበቀለው:: እንደ ዝንብ ይቆጥርህ የነበረው ሸይጧን ከቅጣቱ በኋላ ካንተ መቅረብ እንደሚፈራ አረጋግጥልሃለሁ:: ምናልባት የመበቀል እቅድህ ሶላት ያለፈብህን ቀን በፆም ማሳለፍ ሊሆን ይችላል:: ወይም ደግሞ ከዕለታዊ የቁርአን ፕሮግራምህ አንድ ጁዝእ ተጨማሪ መቅራትም ይሆናል:: ወይንም ነፍስህ የሚከብዳትን ዒባዳ መርጠህ ያን ቀን

መፈፀምም ሌላኛው አማራጭ ነው። የምትወስደው እርምጃ ከባድ በሆነ ቁጥር ሸይጧን ይበልጥ ካንተ ይርቃል። ለየትኛውም የሸይጧን ምት በሌላ ጠንካራ ምት ምላሽ ስጥ። የትኛውንም ከአላህ ትዕዛዝ መዘናጋት በመንቃት ተካ። ውድቀትህን ተስፈንጥረህ በመነሳት አካክስ። ያኔ ከሸይጧን ደባ ትድናለህ፤ ከሚያደርሰው ጉዳት ትገላገላለህ። አደራ! አደራ! እንዳትለማመጠው። ከተለማመጥከው የመዋረድህ ምልክት፣ የፍርሃትህ ማሳያና የሽንፈትህ መጀመሪያ ይሆናልና።

የዚህ ኡምማ ታማኝ የሆኑት አቢ. ዑበይዳ ኢብኑ አልጀራህ (ረ.ዐ.) ለውስጥህ ተስፋን የሚቸር ምክራቸውን ይለግሱሃል፦ "የቆዩ ወንጀሎቻችሁን በአዳዲስ መልካም ሥራዎች አስከትሉ። ከናንተ አንዳችሁ ከምድር እስከ ሰማይ የሞላ ኀጢአትን ቢሰራና ተውባ አድርጎ አንድ መልካም ስራ ቢያስከትል መልካም ስራዋ በኀጢያቶቹ ላይ ድል ትቀዳጃለች።"

ዐብዱላህ ኢብኑ ዑመርም (ረ.ዐ) ተመሳሳይ ምክራቸውን ይለግሳሉ። በእርግጥ ኢብኑ ዑመር (ረ.ዐ.) ከንግግር ምክር ይልቅ የተግባር ምክርን ይመርጡ ነበር። ታዲያ ተግባራዊ ምክራቸው እንዲህ ነበር፦ የአንድ ሶላት ጀመዓ ካለፋቸው ቀጣዩ የሶላት ሰዓት ድረስ ትርፍ ሶላቶችን ይሰግዱ ነበር። ይህንን የሚያደርጉት ሸይጧንን ለመበቀልና ስርዓት ለማስያዝ እንደሆነ ይገልፃሉ።

## *9) የትዕግስትን መጨረሻ አስታውስ*

የምንዳውን ጥፍጥና ያወቀ የሱብርን (የትእግስትን) ምሬት ይቋቋማል። ፈጣንና አስተዋይ ህሊና ያለው ሰው በዙሪያው ያሉ ነገሮችን ይማርባቸዋል። ነጭ ዳቦ የተገኘው ፊቱ የጠቆረ ጋጋሪ በመኖሩ መሆኑን ይገነዘባል። ውዱ አልማዝ የቆነጃጅት አንገት ላይ መንጠልጠል የቻለው ጥልቅ ባህር ውስጥ የዋኙና መከራን ያስተናገዱ ሰዎች በመኖራቸው ነው። የሌሊት እንቅልፍ ያጡ ከፍ ያለ ደረጃን ይቆናጠጣሉ። በዚህች ዓለም ከእንቅልፍ ጋር የተጎዳኙ የእውነት እንቅልፍ ጊዜ (በሞት ጊዜ) ብቸኝነትን ይወርሳሉ። የጥንቸል ስጋ ሐላል የሚሆነው አድኖ ማረድ ከተቻለ ብቻ ነው። ስጋው ጣፍጦ ሊበላ የሚችለው ደግሞ በእሳት ሲጠበስ



CamScanner

ነው:: የሻማ ብርሃን የተገኘው ሻማዋ በመቃጠሏ ነው:: የንግድ ቅፍለቱ ሩቅ በተጓዘ ቁጥር የትርፍ መጠኑ ይጨምራል:: ዕቃዋ እጅግ በጣም ውድ በሆነች ቁጥር ከፍ ያለ ወኔን ትጠይቃለች:: ቀዳሚው የትዕግስት መምህር ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ያደረሱት ጥሪ እንዲህ የሚል ነበር፦

ألا إن سلعة الله غاليه ألا إن سلعة الله الجنة

"አዋጅ! የአላህ ሸቀጥ እጅግ ውድ ነች፤ የአላህ ሸቀጥ እርሷ ጀነት ነች::"[1]

ይህንን የነቢይህን ቃል ሁሌም የምታስታውስ ከሆነ ከተኛህበት ጥልቅ እንቅልፍ መንቃት ይቻልሃል:: የአውራ ዶሮ የሌሊት ድምጽ ይቀሰቅስሃል:: አልያ ግን አውራ ዶሮዎቹ ካንተ የተሻሉ ናቸው::

ወንድሜ እንነሳ ይሳካ ህልማችን፤
ወደ ፊት እንገስግስ አባረን እንቅልፍን፤
አውራ ዶሮ ጮኸ ጥሪ አስተላለፈ፤
እርሱ ከኛ ልቆ በንቃት ከነፈ::

---

አቡ ነዒምና አል-ሓኪም

# የስምምነቱ መጨረሻ

የስምምነቱ ተካፋይ ወንድሜ ሆይ!

የሚከተሉትን መስመሮች በጥሞና አንብብና የስምምነቱ ሰነድ ላይ ሙሉ ሃሳቡን አካትተው፡፡

ኢማም አቡ ሓሚድ አልገዛሊ እንዲህ ይላሉ፡-

“ጥቃቅን ወንጀሎች ወደ ትልቅነት የሚቀየሩባቸው ምክንያቶች እንዳሉ እወቅ፡፡ ከነኚህ ምክንያቶች አንዱ በወንጀሉ ላይ ለረጅም ጊዜ መቆየት ነው፡፡ ለዚህ ነው ‹ለረጅም ጊዜ የሚፈፀም እስከሆነ ድረስ ትንሽ የሚባል ወንጀል የለም፡፡ የአላህ ምህረት እስከተጠየቀና ተውባ እስከ ተደረገበት ድረስ ትልቅ የሚባል ወንጀል የለም” የሚባለው፡፡ አንድ ትልቅ ወንጀል ተሰርቶ እስከመጨረሻው የሚቆምና ተውባ የሚደረግበት ከሆነ ያለማቋረጥና ተደጋግሞ ከሚሠራው ትንሽ ወንጀል የበለጠ የአላህን ይቅርታ የማግኘት ተስፋው ከፍ ያለ ነው፡፡ ምሳሌው ወዲህ ነው፡- በተከታታይ የሚንጠባጠብ የውሃ ጠብታ ለረጅም ጊዜ ድንጋይ ላይ ቢያርፍ ድንጋዩ ላይ የሚታይ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡ የተንጠባጠበውን ያህል ውሃ በአንዴ ድንጋዩ ላይ እንዲፈስበት ቢደረግ ግን ምንም ዓይነት ተፅዕኖ አይኖረውም፡፡ ለዚህ ነበር ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ማለታቸው፡-

((خير الأعمال أدومها وإن قل))

“ከመልካም ሥራ ሁሉ ተመራጩ ዘውትሮ የሚሠራ ሥራ ነው፡፡ ጥቂትም ቢሆን እንኳ፡፡”

“ነገሮች በተቃራኒያቸው ግልፅ ይሆናሉ” እንደሚባለው ጥቂት ሆኖ ለረጅም ጊዜ የሚሠራ መልካም ሥራ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ሲሆን በብዛት ተሰርቶ የሚቋረጥ መልካም ሥራ ደግሞ በልብ ላይ ያለው በጎ ተፅእኖ አነስተኛ ነው፡፡ ልብን ብሩህና ፅዱዕ ከማድረግ አንፃር

የመጀመሪያው ዓይነት መልካም ሥራ የላቀ ሚና አለው። በአንፃሩ ትንሽ ወንጀል በተደጋጋሚ የሚፈፀም ከሆነ ልብን የማጨለምና ፅዱእነቱን የማቆሸሽ አቅሙ የጎለበተ ይሆናል።”

# መዓረፊያ

## 1



وَإِنَّ لَكُمْ فِي الْأَنْعَامِ لَعِبْرَةً

‹‹በእንስሳትም ትምህርት ስጭ (ተዓምር) አለላችሁ።››

(ሱ'ን-ነሕል፡ 66)

## ለጉዞ የሰለጠነች ግመል

ረጅም የበረሃ ጉዞንና የስንቅ እጥረትን መቋቋም በመቻሏ ክብርን ልትጎናፀፍ በቃች። በጌጣጌጥ ልታሸበርቅ ተገባች። ዕድሜዋን በሙሉ በክብር ታሳልፋለች። እስከ ዕለተ ሞቷ ድረስ። ዋጋዋም እጅግ ውድ ሆነ። በአንጻሩ ሌላዋ ግመል መከራን መሸከም የማትችል ትዕግስት አልባ በመሆኗ ዋጋዋ ርካሽ ነው። ስለዚህም፤ የምትቀለበው ለመበላት ሲሆን የምትከበረውም ለመታረድ ነው። ለዚህች ግመል የሚሰጠው ከፍተኛው የማክበር ደረጃ በእርድ ሰዓት ቢላዋውን ከዓይኗ መሰወር ብቻ ነው።

## አዞ

ተመግቦ ሲያበቃ አፉን በሰፊው ይከፍታል። በጥርሶቹ መካከል የተሰነቀሩ የስጋ ቅሪቶችን ታስወግድለት ዘንድ ለትንሿ ድንቢጥ መፍቀዱ ነው። ያንን ካላደረገ ጥርሱ በትላትል እንዳይጠቃ ያሰጋልና።

አንዳንድ ሰዎች ሰብዕናቸው ለዘመናት በትላትል እየተበላ ትላትሉን ከስሩ መንቀል ለሚችል አንድም ሰው ፈቃደኛ አይሆኑም። እንዲህ ዓይነት ሰዎች እንደ አዞውም አልሆኑም የትንሿን ወፍ ሚናም አልተጫወቱም።

ወንድሜ ሆይ! መልካም ነገር ፈፃሚ መሆን ካልቻልክ መልካም ነገር ባንተ ላይ እንዲፈፀም ፍቀድ። ንግግር ማድረግ ካልቻልክ ንግግሩ ቦታ ላይ ተገኝ። ማስተማር ካልቻልክ ተማር። ሌሎችን ለመግራት አቅሙ ባይኖርህ ሌሎች አንተን እንዲገሩህ ፈቃደኛ ሁን።

## የሰለጠነ እርግብ

ባለቤቱ አንገቱ ላይ መልእክት አንጠልጥሎ ሩቅ ቦታ ይልከዋል። መልእክቱን ለማድረስ ጠራራ ፀሐይ፣ ንፋስ፣ ዝናብ፣ ብልጭታና መብረቅን ተቋቁሞ ሌት ተቀን ይጓዛል፤ የአዳኞች ቀስት እንዳያገኘው ከፍ ብሎ ይበራል። ከዚህም በተጨማሪ ምድር ላይ የወደቀችን የስንዴ ፍሬ ለማንሳት ፈፅሞ ወደታች አይወርድም። ምክንያቱም ይህች የስንዴ ፍሬ

ጉዞውን ለማደናቀፍ እንደወጥመድ ልታገለግል ትችላለችና:: ያ ከሆነ ደግሞ መልእክቱ የሚፈለገው ቦታ ሳይደርስ መቅረቱ ነው:: መልእክቱን ካደረሰ በኋላ ግን ክንፉን ዘና አድርጎ ይለቅና እንዳሻው ይበራል:: ትላልቅ ቋጥኞች ላይ በማረፍም ያገኘውን ያህል ይመገባል::

የአላህን መልዕክት የተሸከምከው አማኝ ሆይ! መልእክቱን በማድረስ ሂደት ላይ ምን ያህል ችግር ደረሰብህ? ምን ያህል ከፍታ ወደላይ ወጣህ? ምን መሰናክል አጋጠመህ? የሰው ልጅ ሆይ! ለቅፅበት ያህል ጀነት ውስጥ መነከር የእድሜ ልክ ስቃይን እንደሚያስረሳ አስታውስ:: እርሷ ውስጥ ለሰከንዶች መቆየት ከዱንያና ዱንያ ውስጥ ካሉ መልካም ነገሮች ሁሉ ይልቃል:: ታዲያ ማመንታትህ ለምንድነው?

***ድመት***

ለአንድ ጊዜ ብቻ ውለታ ብትውልላት ባየችህ ቁጥር ትተሻሽሃለች:: ምናልባት የሰጠሃት ትንሽዬ ወተት ይሆናል:: ዳሩ ግን ውለታህን አትረሳም:: ይበልጥ ወደ አንተ ትቀርባለች::

የአካልህ እያንዳንዱ ክፍል የአላህን ውለታ ይመሰክራል:: እያንዳንዱ ፀጉርህ በእሱ ፀጋ የተሸፈነች ነች:: ይህ ሁሉ ሆኖም አላህ ሲፈልግህ ፊትህን ወደ ሌላ ታዞራለህ፤ ወደ እርሱ ባቀረበህ ቁጥር ትርቃለህ፤ በቀጠለህ ቁጥር ሌላን በመውደድ ትቆርጣለህ፤ እርሱ እጅግ በጣም የሚያስፈልግህ ሆኖ እያለ አንተ ግን እርሱን ሞገትክ፤ እርሱ ካንተ የተብቃቃ ሆኖ እያለ እርቅህን ፈለገ:: ከዚህች እንስሳ ለምን አትማርም? ራስህን ከፍ ከፍ አታድርግ፤ ቃቢል ወንድሙን ሃቢልን እንዴት መቅበር እንዳለበት የተማረው ከአሞራ ነው፤ ሱለይማን ስለ ንግስት ቢልቂስ መረጃ ያገኙት ከሁድሁድ ወፍ ነው::

***ጉንዳን***

አካሉ ትንሽ፣ አቅሙ ደካማ ቢሆንም በክረምት ወራት የክብደቱን ብዙ እጥፍ የሚሆን ምግብ ይሸከማል፤ ለበጋ የሚያስፈልገውን ያህል ምግብ ያከማቻል:: ይህንን ሲፈፅም የክረምት ጥፍጥና ወቅት ለበጋው

ስንቅ ከማጠራቀም አላታለለውም። ምክንያቱም በጋ ላይ ያለውን አስከፊ ረሃብ ያውቃልና፤ በበጋ በምግብ እጥረት ያለቁ ወገኖችን ያስታውሳልና።

ወንድሜ! እባክህን ይህንን እውነታ ተገንዘብ! ዱንያ ክረምት ስትሆን አኼራ ደግሞ በጋ ነች። ትንሽ ካስተነተንክና እውነታውን ከተረዳህ የጌታህን እዝነት ታገኛለህ።

## ***አህያ***

በድቅድቅ ጨለማ ወደ አሳዳሪው ቤት ቢላክ ቤቱን አይስትም። በመንገድ ላይ ችግር ካላጋጠመው ያለ ጠቋሚ መድረስ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ አሳዳሪው እሱን ለማስቆም ወይም ፍጥነቱን ለማስጨመር የሚጠቀምበትን ድምፅ ለይቶ ያውቃል።

የጀነትን መንድ የሳትክ፤ የጀነትንና የጀሃነምን ጥሪ ድምፅ መለየት የተሳነህ ወንድሜ ሆይ! ምነዋ የአህያን ያህል ግንዛቤ አጠረህ? መረዳት ሲገባህ ግራ መጋባትህ፤ ወደ ቀብር በቀረብክ ቁጥር መዘናጋትህ፤ የህይወት ፍፃሜ በደረሰ ቁጥር ምኞትህ መርዘሙ፤ እጅግ የምትወዳቸውን ሰዎች በየጊዜው ወደ አኼራ እየሸኘህ አንተ ግን የዱንያን ክብር መሻትህ ለምን ይሆን?!

## ***ልቅ እንስሳ***

ስጋው የማይበላ የእንስሳ ዓይነት ነው። ነጃሳ ምግብ ባህሉ በመሆኑ ስጋው የተበላሸ ነው። የኢስላም ምሁራን “ለአርባ ተከታታይ ቀናት ታስሮ ጥሩ ምግብ እስካልተመገበ ድረስ ስጋውን መመገብ ሐራም ነው።” ብለዋል። ለአርባ ቀናት ጥሩ ምግብ ከተመገበ ስጋው ይፀዳና መብላቱም ይፈቀዳል።

በርካታ ሰዎች በሐራም ውስጥ በመስጠማቸው ምክንያት ባህሪያቸው ይበላሻል። ስጋቸውም ይቆሸሻል። እንኚህ ግለሰቦች እንደዚህ እንስሳ መታሰር ያስፈልጋቸዋል። በእስር ጊዜአቸው መልካም ንግግርንና ደጋግ ስራዎችን መመገብ ይኖርባቸዋል። ያኔ ነፍሳቸው ትፀዳለች፤

ሩሓቸውም ትመጥቃለች:: ስለሆነም፤ መልካም ሁኔታ ላይ ያሉ ሰዎች ብቻ ሊገቡባት የሚችሉትን ጀነት የመግባት ዕድል ይቀዳጃሉ::

﴿ ٱلَّذِينَ تَتَوَفَّىٰهُمُ ٱلْمَلَٰٓئِكَةُ طَيِّبِينَ ﴾ النحل: ٣٢

"እነዚህ መልካም ሁኔታ ላይ ኾነው መላእክት የሚገድሏቸው..."*(አን-ነሕል፡ 32)*

ጀነት ውስጥ በመላኢኮች የሚያምር ድምፅ ጆሯቸው ይደሰታል፤ መንፈሳቸው ይሰክናል፡-

﴿ سَلَٰمٌ عَلَيْكُمْ طِبْتُمْ فَٱدْخُلُوهَا خَٰلِدِينَ ﴾ الزمر: ٧٣

‹ሰላም በናንተ ላይ ይሁን፤ ተዋባችሁ፤ ዘውታሪዎች ሆናችሁ ግቧት::› *(አዝ-ዙመር፡ 73)*

***አንዳንድ ሰዎች*** የሰው ልጅ ሆነው ሳለ የእንስሳ አምሳያ የሆኑ አሉ:: የአደም ልጅ ቅርጽ ይዘው ሳለ የሰው ያልሆነ ባሕሪ የገነቡ አሉ::

***ከነዚም መካከል የአህያ አምሳያ አለ*** በታሰረበት ችካል ዙሪያ ብቻ ይሽከረከራል:: አንድ እርምጃ ወደ ፊት መራመድ አይችልም:: አኼራን ፊትቶ ዱንያን አግብቷል:: የቀን ደነዝ የሌሊት እንጨት ነው:: እንስሶችን ከዚህ መሰል ሰው ይበልጥ ከፍ ያደረገ ጌታ ምስጋና ይገባው:: እነርሱ ቢያንስ ሌሎችን ይጠቅማሉ:: ይህ ሰው ግን ራሱንም ሌላውንም አይጠቅምም:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ነው ያላቸው::

﴿ إِنْ هُمْ إِلَّا كَٱلْأَنْعَٰمِ بَلْ هُمْ أَضَلُّ سَبِيلًا ﴾ الفرقان: ٤٤

«እነርሱ እንደ እንስሳዎች እንጂ ሌላ አይደሉም፤ ከቶውንም ከነሱ ይልቅ መንገድን የተሳሳቱ ናቸው::» *(አል-ፉርቃን፡ 44)*

***<u>የሐር ትል አምሳያ</u>***



CamScanner

የሚሞተው ድር በማድራት ላይ እያለ ነው:: በደመነፍስ ስሜቱና በሰውየው መካከል ያለው ትስስር አስገራሚ ነው፤ በሸይጧኑና በእርሱ መካከል ያለው ፍቅር አስደማሚ ነው:: ህይወቱን የሚያጠፋው በገዛ እጁ ነው:: ወደ ጀሀነም በፈቃዱ ይጓዛል:: እንዲህ ዓይነት ሰዎችን አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላቸዋል፡-

﴿ يُهْلِكُونَ أَنفُسَهُمْ ﴾ التوبة: ٤٢

‹ነፍሶቻቸውን ያጠፋሉ::› *(አት-ተውባ፡ 42)*

## *የሰጎን አምሳያ*

አሸዋ ውስጥ ጭንቅላቱን ይቀብራል፤ የሚሰራውን ግፍና ወንጀል ማንም ሰው አያውቅብኝም ብሎ ያስባል:: እጁ በንፁሃን ደም ጨቅይቶ ማንንም እንዳልገደለ ይምላል፤ የጣቱ አሻራ የወንጀሉን ቦታ እየጠቆመ አንድም ንብረት እንዳልሰረቀ ይከራከራል፤ አፉ ላይ የአስካሪ መጠጥ እንጥብጣቢ እየታየ አላህን በሚፈሩ ደጋግ ባሮች ካባ ተሸፍኖ ይቀርባል:: እንዲህ ዓይነቶቹ ግለሰቦች፡-

﴿ يُخَٰدِعُونَ ٱللَّهَ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَمَا يَخْدَعُونَ إِلَّآ أَنفُسَهُمْ وَمَا يَشْعُرُونَ ﴾ البقرة: ٩

"አላህንና እነዚያን ያመኑትን (ሰዎች) ያታልላሉ፤ የማያውቁ ሲሆኑ ነፍሶቻቸውን እንጅ ሌላን *አያታልሉም::" (አል-በቀራ፡ 9)*

## *የእስስት አምሳያ*

በፍጥነት በሚለዋወጥ ባህሪው ይታወቃል፤ ደጋግ ሰዎች ጋር ሲሆን የቁርኣን አንቀፆችን በተመስጦ ያነበንባል፤ ከተቃራኒ ሰዎች ጋር በሚሆንበት ጊዜ ሙዚቃና ጭፈራ ያስደምመዋል፤ የአላህን አብሮነት ተከልክሏል፤ ወጥ የሆነ ሰብዕና የለውምና! የህይወት ጎዳናቸው በሚከተለው የቁርኣን አንቀጽ ይገለፃል፡-

﴿ مُّذَبْذَبِينَ بَيْنَ ذَٰلِكَ لَآ إِلَىٰ هَٰٓؤُلَآءِ وَلَآ إِلَىٰ هَٰٓؤُلَآءِ ﴾ النساء: ١٤٣



CamScanner

"በዚህ መካከል ወላዋዮች ሆነው ወደነዚህም ወደነዚያ አይደሉም።" *(አን-ኒሳእ፡ 143)*

## *የሴሊት ወፍ አምሳያ*

አፈጣጠሩ ወጣ ያለ ነው፤ ጨለማን በእጅጉ ያፈቅራል፣ ብርሃንን ይጠላል። ወንጀልን የማጣጣምና መልካም ሥራን የመጠየፍ በሽታ ተጠናውቶታል፤ ተፈጥሮው የተገለበጠ በመሆኑ አስተሳሰቡም የተገለበጠ ነው። ስለሆነም:-

﴿ وَإِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَحْدَهُ ٱشْمَأَزَّتْ قُلُوبُ ٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِٱلْـَٔاخِرَةِ ۖ وَإِذَا ذُكِرَ ٱلَّذِينَ مِن دُونِهِۦٓ إِذَا هُمْ يَسْتَبْشِرُونَ ﴾ الزمر: ٤٥

"አላህም ብቻውን በተወሳ ጊዜ የነዚያ በመጨረሻይቱ ዓለም የማያምኑ ሰዎች ልቦች ይሸማቀቃሉ (ይደነብራሉ)። እነዚያም ከርሱ ሌላ የሆኑት (ጣዖታት) በተወሱ ጊዜ እነርሱ ወዲያውኑ ይደሰታሉ።" *(አዝ-ዙመር፡ 45)*

# 3

## ስምምነት ሦስት

# የተሰናባች ሶላት ስገድ



ኢመናዊ ቆይታ

ሶላት ውስጥ ሆነህ የምትዘነጋ ሰው ሆይ! አካልህ እዚህ ነው፤ ልብህ ሀገሩን ሁሉ ያዳርሳል። ሶላትህ ሩህ የሌለው በድን፤ ሕይወት የሌለው አካል ነው፡፡ የምታነበውን አትረዳውም። የአንተ ምሳሌ ወዲህ ነው፡- ንጉሱን ለማግኘት ውድ ስጦታ እንዲያበረክት እንደተነገረው ሰው። ሰውዬው ስጦታውን እንዲያስቀምጥ የተነገረው የእንግዳ መቀበያ ሳሎን ውስጥ ነበር፡፡ ታዲያ ይህ ሰው እፍኝ አፈር ዘገነና በስጦታ ወረቀት ጠቅልሎ ሳሎን ውስጥ አስቀመጠ፡፡ ገፀ-በረከቱንም ለንጉሱ አበረከተ፡፡ ንጉሱ ስጦታውን ከፍቶ ሲመለከት በእጅጉ ተቆጣ፤ የሰውዬው እጣ ፋንታ ወደ ንጉሱ ከመቅረብ ይልቅ መራቅና መባረር ሆነ፡፡

## አምስቱ ደረጃዎች፡-

ኢማም ኢብኑልቀይም እንዲህ ይላሉ፥ "ሰዎች በሶላታቸው መሠረት በአምስት ደረጃ ይከፈላሉ፡-

*አንደኛው፡-* ራሱን በእጅጉ የበደለና ድንበር ያለፈ ሰው ነው። የዚህ ዓይነቱ ግለሰብ የሶላቷን ቅድመ ሁኔታ –ዉዱእ ያጓደለ፣ ወቅቶቿን ያልጠበቀና ግዴታዎቿን በትክክል ያላሟላ ሰው ነው።

*ሁለተኛው፡-* የሶላትን ወቅቶቿን፣ ሕግጋቷንና ግልጽ የሆኑ ማእዘናቶቿን የሚያከብር ሲሆን ነገር ግን ነፍሱ ከሸይጧን የሚደርስባትን ጉትጎታ ከመታገል ይልቅ ከጉትጎታውና ዓለማዊ ሀሳቡ ጋር የሚነጉደው ነው።

*ሦስተኛው፡-* የሶላትን ህግጋቶች በትክክል የጠበቀ ሲሆን ነፍሱ የሚደርስባትን የሸይጧን ውትወታና ምድራዊ ሃሳብ ለመቋቋም ትግል ላይ ነው። ይህ ሰው ሶላቱ እንዳይሰረቅበት ለመከላከል ትግል ላይ በመሆን፤ በሶላትና በትግል መካከል ሶላቱን ይፈጽማል።

*አራተኛው፡-* ሶላት ውስጥ በሚገባበት ጊዜ የሶላቷን ግዴታዎችና ህግጋቶች በትክክል ያሟላል። ልቡ የሶላቷን ሐቆች ላለማጉደል በከፍተኛ ጥንቃቄ ይጠመዳል። አንዳች ጉድለት እንዳይኖር የተቻለውን ያደርጋል። ዋነኛ ሀሳቡ ሶላቱ እጅግ የተሟላችና የተዋበች እንድትሆን ማድረግ ነው። ልቡ የተጠመደው በሶላቱ ጉዳይና በጌታው አምልኮ ላይ ብቻ ነው።

*አምስተኛው፡-* ሶላት ውስጥ ሲገባ በተሟላ ሁኔታ ይሆናል። ለየት የሚያደርገው ልቡን ሙሉ ለሙሉ ከጌታው ፊት ማስቀመጡ ነው። በልቡ ወደ እርሱ ይመለከታል። እንደሚከታተለው ይሰማዋል። በጌታው ፍቅርና ልዕልና ሙሉ ልቦናው ተሞልቷል። አላህን

(ሱ.ወ.) የሚያየው ያህል ይሰማዋል። የሸይጧን ውትወታዎችና ውልብታዎች በዚህ ልዩ የአምልኮት ስሜት ውስጥ ይጠፋሉ። በጌታውና በእርሱ መካከል ያለው ግርዶሽ ይነሳል። የዚህ ዓይነቱ ሰው ሶላትና ፍፁም መዘናጋት ውስጥ ሆኖ የሚሰግድ ሰው ሶላት የሚበላለጡት የሰማይና የምድር ያህል ነው። ምክንያቱም ይህ ሰው ሙሉ ሀሳቡ ጌታው ዘንድ የሆነና በሶላቱም ዐይኑ ያረፈ ሰው ነውና!

(በዚሁ መነሻነት ስለ አምስቱ ሰዎች ሶላት እንዲህ ማለት ይቻላል)፡-

የመጀመሪያው ዓይነት ሰው ይቀጣል፤ ሁለተኛው ይመረመራል፤ ሶስተኛው ይቅር ይባላል፤ አራተኛው ይመነዳል፤ አምስተኛው ወደ ጌታው የተቃረበ ይሆናል።"



CS CamScanner

# የስምምነቱ ትርፎች

## 1. በሶላት መርካት

አላህን የሚፈራ ሰው በሶላቱ ይረካል፤ ጌታውን በማናገሩ ብቸኝነቱ ይወገድለታል:: በሶላቱ በመመሠጡ ምክኒያት ሶላቱም ሳይታወቀው ያልቅበታል:: “አላህ ጋር የምታሳልፈው አንድ ዓመት የቅጽበት ያህል ነው” እንደሚባለው ነው::

የመሠላቸትና የመዘናጋት በሽታ ካጠቃውና የአላህ ፍራቻ ከልቡ ከራቀ በዚህ ሁኔታ የሚያሳልፋቸው ሰዓታት የአመታት ያህል ይረዝሙበታል:: “ከአላህ ርቀህ የምታሳልፋት ቅፅበት የአንድ ዓመት ያህል ነች::” እንደሚባለው መሆኑ ነው::

አላህን መፍራት ሶላት ለባሪያው እንድትቀለውና ያለምንም ጫና እንዲፈፅማት ያስችለዋል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል:-

﴿وَإِنَّهَا لَكَبِيرَةٌ إِلَّا عَلَى الْخَاشِعِينَ﴾ البقرة: ٤٥

“እርሷም (ሶላት) በፈሪዎች ላይ እንጅ በሌላው ላይ በእርግጥ ከባድ ናት::” *(አል-በቀራህ:- 45)*

ይልቁንም ሶላትን ልዩ የደስታ፣ የእርካታና የመረጋጋት ምንጭ ያደርጋታል:: ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን አስመልክተው እንዲህ ይላሉ:-

«وجعلت قرة عيني في الصلاة» (احمد والنسائي)

“የዐይን ማረፊያዬ በሶላት ውስጥ ተደርጎልኛል::”[1]

---

[1] አህመድና ነሳኢ

እናም አላህን መፍራት በሚፈጥረው ልዩ ድባብ የተነሳ መስጂዶች በአራት ማዕዘን የተከለሉ ጀነቶች ይሆናሉ። በውስጣቸው የመንፈስ እርካታና የህሊና ሰላም ይገኝባቸዋል።

በኹሹእ (አላህን በመፍራት) የምትሰገድ ሶላት የምትፈጥረው እርካታ ዱንያ ላይ እየሆነ ያለን ነገር ሁሉ እስከመርሳት ሊያደርስ እንደሚችል ከሚያሳዩ ታሪካዊ እውነታዎች መካከል የዑርዋ ኢብኑ አዝ-ዙበይር (ረ.ዐ.) ታሪክ ይታወሳል። ይህች ተመስጦና እርካታ በእኚህ ታላቅ ሰው ህይወት ተስተውላለች። ይህች የደስታ ባህር የስቃይ መርከብን አስጥማ አስቀርታለች። መርከቧ የአካልና የስሜትን ዳርቻ ሳትደርስ ተውጣለች። እንዲያ ሊሆን የቻለው እንዴት ይሆን?

ጋንግሪን የተባለ በሽታ የዑርዋን እግር አጠቃ። ቀሪውን አካል ከበሽታው ለመታደግ ሲባል በሽተኛው እግር መቆረጥ እንዳለበት ሃኪሞች ውሳኔ ላይ ደረሱ። ዑርዋ ኢብኑ አዝዙበይር በውሳኔው ተስማሙ። ሶላት ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ እግራቸውን እንዲቆረጡ ለሃኪሞች ጠቆሙ። ዑርዋ ለሶላት ቆሙ። በኹሹዓቸው (አላህን መፍራት በተሞላው ሶላታቸው) ከሰዎች ዓለም ወጡ። ወደ አላህ (ሱ.ወ) በመቅረብ የሚገኘው እርካታ ውስጥ ገቡ፤ ሀኪሞቹ የዑርዋን ቁርጭምጭሚት በቢላዋ መቁረጥ ጀመሩ። ዑርዋ ዘወርም አላሉ። ቢላዋው አጥንታቸው ጋር ሲደርስ ሀኪሞቹ መጋዝ መጠቀም ነበረባቸው። በመጋዝ መገዝገዝ ያዙ፤ እግራቸውም ተቆረጠ። ዑርዋ ምንም ዓይነት የመወራጨት ስሜት አላሳዩም። እግራቸው ከተቆረጠ በኋላ በዘመናቸው በነበረው የህክምና ዕውቀት መሠረት ደሙን ለማስቆም የተቆረጠው እግራቸው የፈላ ዘይት ውስጥ ተነከረ። ያኔ ዑርዋ ራሳቸውን ስተው ወደቁ፤ ለሰዓታት ራሳቸውን ስተው ከቆዩ በኋላ ሲነቁ "ጨረሳችሁ እንዴ?" ነበር ያሉት።

## *2. <u>ቢላል ሆይ! በእርሷ አሳርፈን</u>*

ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ከባድና የሚያሳስብ ጉዳይ ሲያጋጥማቸው ወደ ሶላት ይጣደፉ ነበር። የሰዎች ክፉ ምግባር ሲያስቸግራቸው፣

የሚያደርሱባቸው ጉዳትና ደባ ሲያደክማቸው ቢላልን እንዲህ በማለት ይጠሩታል፦

«يا بلال أقم الصلاة، أرحنابها» (احمد وابوداود)

"ቢላል ሆይ! ለሶላት ኢቃም አድርግና በእርሷ አሳርፈን"[1]

ይህች ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚሏት እረፍት የላይ ላይ እንቅስቃሴና ከአንገት የማያልፍ ማነብነብን ተከትላ አትገኝም:: የአላህን አንቀጾች የሚያስተነትንና በእርሷ ውስጥ የሚኖር ሙእሚን ሃብት ነች:: ያኔ አንድን አማኝ ካለበት ሀዘንና ጭንቀት ፈልቅቃ ታወጣዋለች፤ ወደ ኢስላማዊና በኢማን ወደ ተሞላው አየር ታጓጉዘዋለች:: ከስቃይ ዓለም አውጥታ ወደ ምንዳ አለም ታሸጋግረዋለች:: ከጠባብና ድፍርሷ ዱንያ አርቃ ወደ ዕዱዕና ሰፊዋ አኼራ ታቀርበዋለች::

በኹሹዕ[2] የተሠገደች ሶላት የእዝነት ዳበሳ ነች:: በእርሷ ምክንያት ድካምና ስቃይ በኢማናዊ እርካታ ውስጥ ይሸሸጋል፤ ፍፁም የመንፈስ ልዕልና ይሰፍናል:: ለነፍስ ጭንቀትና ድክመት ፍቱን መድሃኒት ነች:: አላህን በማስታወስ ልቦች ይረጋጋሉና! ከከፍተኛ የውስጥ ነውጥ በኋላ ልብ ትረጋጋለች፤ የመረጋጋትና እርካታ ምንጭ ከሆነው ጌታ ጋር ተገናኝታለችና! ከድንጋጤና ከፍርሃት ትገላገላለች፤ ሲሳዩዋና ዕድሜዋ በእጁ ከሆነው ጌታዋ ዘንድ ቆማለችና! ከስጋት ወጥታ ትስክናለች፤ አላህ (ሱ.ወ) ከወሰነው ውጭ ምንም ዓይነት ችግር አይደርስባትምና!

### *3. ምንዳው በኹሹዕ ልክ ነው*

አንድ ግለሰብ ከሶላቱ የሚያገኘው ምንዳ ሶላት ውስጥ ካለው ኹሹዕ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው:: የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን አስመልክተው እንዲህ ብለዋል፦

---

[1] *አህመድና አቡዳውድ*

[2] *አላህን በመፍራትና በተመስጥዖ*

"إن الرجل لينصرف ومايكتب له إلا عشر صلاته، تسعها ثمنها، سبعها، سدسها، خمسها، ربعها، ثلثها، نصفها"

"ሰውየው ሰላቱን ያጠናቅቃል፤ ነገር ግን ከሶላቱ አንድ አስረኛዋን፣ አንድ ዘጠነኛዋን፣ አንድ ስምንተኛዋን፣ አንድ ሠባተኛዋን፣ አንድ ስድስተኛዋን፣ አንድ አምስተኛዋን፣ አንድ አራተኛዋን፣ አንድ ሦስተኛዋን ወይም ግማሿን እንጂ አልተጻፈለትም::"[1]

ከዚህ በመነሳት ኢብኑ ዐባስ (ረ.ዐ.) አንድ እውነታ ያስቀምጣሉ:- "ከሶላትህ የምትመነዳው ልብህ ስብስብ ብሎ የሰገድከውን ያህል ነው::"

## 4. *የወንጀል መማር*

ረሱሉ (ሰ.ዐ.ወ) ያሉትን እነሆ:-

"ما من مسلم يتوضا فيسبغ الوضوء، ثم يقوم فى صلاته فيعلم مايقول، إلا انفتل وهو كيوم ولدته أمه"

"ማንኛውም ሙስሊም በአግባቡ ዉዱእ አዳርሶ፣ ከዛም ሶላት ላይ ቆሞ የሚለውን ያወቀ ከሆነ ሶላቱን ሲያጠናቅቅ እናቱ የወለደችው ዕለት እንደነበረው (ንፁህ) ይሆናል::"[2]

‹ሶላት ውስጥ ሀሳቡን ሰብስቦ የሚለውን የሚያውቅ ሰው ምንዳ ወንጀሉ መማር ነው› የሚለው በኹሹእ መስገድ ያለፈን ወንጀል አስወጋጅና ያለፈን ሀጢአት አውዳሚ መሆኑን እንረዳለን:: በኹሹዕ መንፈስ የምትሰገድ አንዲት ሶላት- ወንድሜ ሆይ!- የልብህን ወለል የማፅዳት አቅም አላት::

አላህን ፈርተው የሚሰግዱ የአላህ ባሮች ትርፋቸው ምንኛ እፁብ ድንቅ ነው?! ስኬታቸውስ ምንኛ ውድ ነው?!

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ያሉትን አስተውል:-

---

አህመድ፣ አቡዳውድና ኢብኑ ሒባን እንደዘገቡት
ሙስሊምና አልሓኪም ዘግበውታል

"إن العبد إذا قام يصلي أتى بذنوبه كلها، فوضعت على رأسه وعاتقيه، فكلما ركع أو سجد تساقطت عنه"

"አንድ ባሪያ ሶላት ለመስገድ በሚቆምበት ጊዜ ወንጀሉ በሙሉ ይመጣና ራሱና ትከሻዎቹ ላይ ይቀመጣል:: ሩኩዕና ሱጁድ ባደረገ ቁጥር ከእሱ እየተንጠባጠበ ይወድቃል::"[1]

ዐብዱረኡፍ አልመናዊ ይህንን ሐዲስ ከኹሹዕ (አላህን ፈርቶ ከመስገድ) ጋር አዛምደው እንዲህ ይላሉ:- "ከሶላቱ አንድ ሩክን (ማዕዘን) አሟልቶ ባጠናቀቀ ቁጥር ከወንጀሉ አንድ ማዕዘን ይወድቃል:: ሁሉንም የሶላቱን ማዕዘናት አሟልቶ ሲፈፅም ሀሉም ወንጀሎቹ ሙሉ ለሙሉ ይወድቃሉ:: ይህ የሚሆነው ቅደመ ሁኔታዋ ማዕዘኗ እና ኹሹዑዋ ለተሟላላት ሰላት ነው:: ‹ባሪያ› እና ‹መቆም› የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ሶላቷ የተሟላችና ለታላቁ ጌታ ተናንሶ መቆምን ነው::

ጦበራኒ፣ አቡ ነዒምና በይሀቂ

# ስምምነቱን የከማካበር ውጤቶች

ዐብዱላህ ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት ያሳስባሉ፡- "ሶላት መስፈሪያ ናት። በትክክል የሰፈረ ያለምንም ጉድለት ምንዳውን ያገኛል። ሚዛን የሰለበ ደግሞ አላህ (ሱ.ወ) ያለውን ያስታውስ።" ይኸውም፡-

﴿ وَيْلٌ لِّلْمُطَفِّفِينَ ﴾ المطففين: ١

"ለሰላቢዎች ወዮውላቸው" *(አል-ሙጠፍፊን፡1)*

ሚዛን ላጎደሉ ሰዎች አላህ (ሱ.ወ.) የሰጠው ማስጠንቀቂያ በሚከተሉት ነጥቦች ይገለፃል፡-

1. ***<u>ምንዳን ማጣት</u>***

የሶላት ቀዳሚ ዓላማ ልብን መሰብሰብና የአላህን ፍራቻ መፍጠር ነው። የምንዳው መሽከርከሪያም ይኼው ነው። አሊያማ በምላስ ማነብነብና አካልን ጎንበስ ቀና ማድረግ ምን ሊፈይድ?! ትልቅ ምንዳ የሚገኘው ተመጣጣኝ ልፋት ሲኖር ነው። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ከዱንያ ጋር ያለን ትስስር በመቁረጥና ሙሉ ሀሳብን አኼራ ላይ በማዋል ነው።

አቡሁረይራ (ረ.ዐ) በዘገቡት ሐዲስ አንድ ሰው መስጅድ ገባ። የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በመስጅዱ አንድ ጎን ላይ ተቀምጠው ነበር። ሰውዬው ሰገደና ወደ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) መጥቶ ሰላምታ አቀረበላቸው። መልእክተኛውም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ መለሱለት፡-

((وعليك السلام فارجع فصل فإنك لم تصل))

‹ሰላም በአንተም ላይ ይሁን፤ ተመለስና ስገድ አልሰገድክምና!› አሉት። ድጋሚ ሰገደና መጥቶ ሰላምታ አቀረበላቸው። አሁንም ‹ሰላም በአንተም ላይ ይሁን፤ ተመለስና ስገድ አልሰገድክምና!›

አሉት:: ሰውዬው ከሁለተኛው ወይም ከሶስተኛው በኋላ እንዲህ አለ:- "አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ያስተምሩኝ" መልእክተኛውም (ሰ.ዐ.ወ) ሶላት አሰጋገድ አስተማሩት:: [1]

## 2. ምንኛ የከፋ መመሳጠር ነው!

ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) አንድ ሰው በፍጥነት ሲሰግድ (ሶላቱን እንደ ዶሮ ሲተከትክ) አስተዋሉትና እንዲህ አሉት:-

((يافلان ألا تتقى الله؟ ألا تنظر كيف تصلى؟ إن أحدكم إذاقام يصلى إنما يقوم يناجى ربه فلينظر كيف يناجيه))

(مسلم والنسائى وابن خزيمة)

"እከሌ ሆይ! አላህን አትፈራምን? እንዴትስ እየሰገድክ እንደሆነ አታስተውልምን? ከናንተ መካከል አንዳችሁ ሶላት ለመስገድ ሲቆም ጌታውን ለማናገር ነው የቆመው:: ስለሆነም እንዴት እያናገረ እንደሆነ ልብ ይበል::"[2]

አንድ ሰጋጅ ወደ ሶላት ሲቆም ጌታውን እያናገረ ነው:: ከምድራዊ ነገስታት አንዱን እያናገረ ቢሆን ኖሮ ሰውነቱ በተንቀጠቀጠ፣ ቆዳው በተጨማተረ፣ የራስ ፀጉሩ በቆመ፣ ለሴኮንድ ያክል ባልተዘናጋና ችላ ባላለ ነበር:: የምድር ላይ ንጉሶች ንግስና በሙሉ ንግስናውን ቅንጣት ታህል የማይወዳደሩት የሆነውን አላህን (ሱ.ወ.) ማናገርስ እንዴት መሆን አለበት?! የዱንያ ነገስታት የዱንያ ግብስባሶ በእጃቸው ማድረግ ችለዋል:: አንተና መሠሎችህ ደግሞ ይህንኑ ፍለጋ እየማሠናችሁ ነው:: በላጩ ነገር የዱንያንም ሆነ የአኼራን ነዋያት በሙሉ በእጁ በሆነው ጌታ ላይ ሙሉ ተስፋህን ማድረግህ ነው:: የዕቃውን ልክና የሽልማቱን ትልቅነት ማወቅህ ነው፤ ያኔ የምትፈልገውን የመጠየቅ ጥበብና የማናገርን ስርዓት ትማራለህ::

ሐሰን አል-በስሪ (ረ.ዐ.) በአንድ ሰው ዘንድ አለፉ:: በጠጠር እየተጫወተ ዱዓእ ያደርጋል:- "ጌታዬ ሆይ! ሑረልዐይን ሚስት አጋባኝ"

---

[1] ቡኻሪና ሙስሊም

[2] ሙስሊም፣ ነሳኢይና ኢብንኹዘይማህ

ይላል:: ሐሰን አልበስሪ ሰውየው ዱዓእ የሚያደርግበት ሁኔታ አልጣማቸውምና እንዲህ አሉት:- "ምንኛ የከፋህ (መጥፎ) እጮኛ ነህ!? በጠጥር እየተጫወትክ ሑረልዐይንን ትጠይቃለህ?!"

## 3. *የስርቆት ወንጀል*

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይሉሃል:-

((أسوأ الناس سرقة الذى يسرق من صلاته لا يتم ركوعها ولا سجودها ولا خشوعها)) (احمد والحاكم)

"ከሰዎች ሁሉ የከፋ ሌባ ማለት ከራሱ ሶላት የሚሰርቅ ሰው ነው:: ሩኩዕዋን፣ ሱጁዷንና ኹሹዐዋን አያሟላም::"[1]

***የከፋ ሌባ ነው. . .*** ምክኒያቱም፤ ከጌታው ፊት ቆሞ ነው የሰረቀው:: በጌታውና በርሱ መካከል ምንም ግርዶሽም ሆነ አስተርጓሚ የለም፤ ታዲያ ሥነ-ሥርዓት መያዙ ቢርቅ ሐያእ (ትሁትነቱ) የትሄደ?!

***የከፋ ሌባ ነው. . .*** ምክንያቱም፤ የሰረቀው የራሱን ሶላት ነው:: ይህን በመፈፀሙ አበላሻት:: ሶላቷ በመበላሸቷ ግን ሁሉም ስራው ይበላሻል:: በመስገዱ ወደ ምንዳ ከመቅረብ ይልቅ በራሱ ላይ ቅጣቱን አቻኮለ::

***የከፋ ሌባ ነው . . .*** ምክንያቱም፤ የዱንያ ቁሳቁስ የሰረቀ ሌባ በሰረቀው ነገር ሊጠቀም ይችላል፤ ይህ ሰው ግን የሰረቀው የራሱ የሆነን ምንዳ ነው፤ በዚህም በአኼራ ቅጣትን ይሸምታል::

በርግጥም ምንኛ የሚያስጠላ ስርቆት ነው?! ምንኛ ከባድ ወንጀል ነው?! አንተ ኹሹዕን ከሶላትህ ውስጥ ያጠፋህ ወንድሜ ሆይ! እስኪ ንገረኝ ሶላት አንተ ዘንድ ክብደት ካጣች ከዲንህ ምን የቀረህ ነገር አለ?! የስራህን አስፀያፍነትና የወንጀልህን ክብደት ማወቅ ከፈለግክ ከዚህ በፊት ባነሳናቸው ነጥቦች ላይ ራስህን ጠይቅ:: በዘመናቸው ለኖረ አንድ ስራ ፈት ኢብኑ አልጀውዚ በገሰፁበት ምክር ራስህን ገስፅ:: እንዲህ ነበር

---

[1] *አህመድ እና ሐኪም*

ያሉት፡- "አንተ ስራ ፈት ሆይ! የንግድ ቅፍለት እየነዳህ ወደ አንድ ሀገር ብትጓዝና ያለምንም ትርፍ ብትመለስ ያጣኸውን ትርፍ እያሰብክ በሀዘን በተብተከተክ ነበር። ስላጠፋኸው ጊዜ በቁጭት በበገንክ ነበር። የዐይን ማረፊያ ወደ ሆነችው ሶላት ውስጥ ገብቶ ምንም ሳይጠቀም የወጣ ሰው ሊያለቅስ አይገባውምን?"

## 4. *ከነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) መንገድ ውጭ የመሞት አደጋ*

አቢ ዐብደላህ አልአሽዐሪይ (ረ.ዐ.) ሲተርኩልን እንዲህ ይላሉ፡- አንድ ሰው ሩኩዑን ሳያሟላ፤ ሱጁዱንም ጥሬ እንደምትለቅም ዶሮ በፍጥነት ደፋ ቀና እያለ ሲሰግድ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ተመለከቱት። እንዲህም አሉ፡-

"لو مات على حاله مات على غيرملة محمد" (الطبراني وابويعلى)

"በዚህ ዓይነት አሰጋገዱ ቢሞት ከሙሐመድ መንገድ ውጭ ሆኖ ሞቷል።"[1]

ይህ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከባድ ማስጠንቀቂያ ነው። ይህ ሰው ይህንን ንግግር ከልቡ ቢሰማ ራሱን ስቶ በወደቀ ነበር። ተራሮች ሊሸከሙት የሚከብድ ንግግር ነው። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሶሃቦቻቸውን ሊያስተምሩ የፈለጉት በሶላት ውስጥ የመረጋጋትና ልብን የመሠብሰብን አስፈላጊነት ነው። ማስጠንቀቂያው ሶላት ውስጥ ሲገቡ ለቦታው ተገቢውን ክብር ለማይሰጡ ሰዎች በሙሉ ነው። መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) ያለ ምንም ብዥታ ወደነርሱ በጣታቸው ይጠቁማሉ፤ ማንነታቸውን ከሌላው ለይተዋል፤ ሌሎች ሰዎች እንደነርሱ እንዳይሆኑም አስጠንቅቀዋል። እንዲህ ይሏቸዋል፡- "በዚህ ሁኔታ ላይ ከሞታችሁ ከእኔ መንገድ ውጭ ሆናችሁ ትሞታላችሁ!"

---

[1] ጦበራኒና አቡ የዕላ

እናም ያለፈ ጥፋታችሁን በቶሎ አርሙ:: የጠፋባችሁን ፈልጋችሁ አግኙ:: ትንፋሻችሁ እስካለች ድረስ የመታደስ እድል አላችሁ:: . . . በልባችሁ ምድረ-በዳ የኢማን ዘር ዝሩ:: ባቡሩ ጥሏችሁ ከመሄዱ በፊት በፍጥነት ድረሱበት:: ማናችሁም ቀብሩ ውስጥ ሩኩዕና ሱጁድ የማድረግ ዕድል የለውምና!

የነቢያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መንገድ ይህ ነው፡- ሶላትን በተሟላ መልኩ መከወን:: የሚያሳዝነው አንድ ሰው ዕድሜ ልኩን ሶላት ሲሰግድ ኖሮ በዕድሜው መጨረሻ ላይ ሶላቱ ሲገመገም በህይወቱ አንዲትም ሶላት በተስተካከለና በተሟላ መልኩ የሰገደው ላይኖረው ይችላል:: ይህንን እውነታ ዑመር ኢብኑል ኸጧብ (ረ.ዐ.) አንድ ቀን ሚንበር ላይ ወጥተው ነበር ያመለከቱት፡- “አንድ ሰው አንዲትም ሶላት በትክክል አሟልቶ ሳይሰግድ በእስልምና ውስጥ ሊያረጅ ይችላል::” ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ሲጠየቁ “ኹሹዑ፣ ለእርሱ መተናነሱና ወደ አላህ (ሱ.ወ.) ፊትን ማዞሩ የተሟላ አልነበረም” በማለት ነበር የመለሱት::

ከዚህም በላይ የዚህ ዓይነቱ ሰው እና መሰሎቹ ሱጁድ አንዳንድ ቀደምት ሰለፎች ‹ወንጀል የምታስከትል ሱጁድ› የሚሏት ዓይነት እስከመሆን ትደረሳለች:: እንዲህ ይላሉ “አንድ ባሪያ ወደ አላህ ለመቃረብ በማሰብ ሱጁድ ያደርጋል:: በዚህች ሱጁድ ላይ የፈፀመው ወንጀል ለከተማው ህዝብ ቢከፋፈል ለጥፋታቸው በቂ ይሆናል::”“እንዴት እንደዚያ ሊሆን ይችላል?” ተብለው ሲጠየቁ፡- “እርሱ ሱጁድ ባደረገበት ቅጽበት ልቡ የዱንያ ስሜቱን በማድመጥ ላይ ነው፤ ርካሽና የተጠላ የሆነን ተግባር በመመልከት ላይ ነው፤ በርግጥም ልቡ ላይ የሐራምና የርካሽ ነገር ፍላጎት ነግሷልና::” በማለት መለሱ::

ኡሙ ሰለማ (ረ.ዐ.) ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዘመን ጀምሮ እስከ ዑሥማን (ረ.ዐ.) ዘመን ድረስ የሶላት ውስጥ ኹሹዑ እንዴት በሂደት እየቀነሰ እንደመጣ ስታስቀምጥ እንዲህ ብላለች፡- “በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን አንድ ሰው ሶላት ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ ዐይኑ ከእግሮቹ መቆሚያ አይነቀልም ነበር:: ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲሞቱ ደግሞ

ሰዎች ለሶላት ሲቆሙ ዐይናቸው የግንባራቸውን ማረፊያ አይለቅም ነበር፡፡ አቡበክርና ዑመር (ረ.ዐ) ሲሞቱ ደግሞ ሰዎች ዐይናቸውን ከቂብላ አቅጣጫ አይነቅሉም ነበር፡፡ በዑሥማን ኢብኑ ዐፋን (ረ.ዐ.) ዘመን ፈተና ተከሰተ፡፡ ሰዎችም ወደ ቀኝና ወደ ግራ መዟዟር ጀመሩ፡፡”

## ከስምምነቱ ሡጤታማነት

ብዙ ጊዜ ልባችን የወንጀል ደመና ያንዣብበታል፤ ያኔ ልብ ይጨልማል፣ ኢማንም ይቀዛቀዛል። የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህንን አስመልክተው ያሉትን አድምጥ፡-

”مامن القلوب قلب إلا وله قلب كسحابة القمر، بينما القمر يضئ إذ عليه سحابة فأظلم، إذانجلت عنه فأضاء“

“ማኛውም ቀልብ በደመና ውስጥ እንደምትወጣ ጨረቃ ዓይነት መለዋወጥ አለው። ጨረቃዋ እያበራች ደመናው ካለ ጨለማ ይነግሳል። ደመናው ሲገፈፍ ብርሃኑ ፍንትው ይላል።”[1]

የሚከለተሉትን መመሪያዎች ከተከተልን በአላህ ፈቃድ ለጨለማው ምክንያት የሆነው ደመና ይገፈፋል።

### 1. ለአዛን ጥሪ ፈጣን ምላሽ ስጥ

እናታችን ዓኢሻ (ረ.ዐ) የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አዛን ሲሰሙ የሚያሳዩትን ባህሪ ስትገልፅ እንዲህ ትላለች፡- “ከኛ ጋር ሲጨዋወቱ (ሲያወሩንና ስናዋራቸው) ይቆዩና የሶላት ሰዓት ሲደርስ እንደማያውቁንና እንደማናውቃቸው ይሆናሉ።”

ኢብራሂም ኢብን መይሙን አልመርዘዊ ይህንኑ አንፀባራቂ መንገድ በመከተል ወርቅና ብር ከሚቀጠቅጥበት ስራው ላይ እያለ አዛን ሲሰማ ያነሳውን መዶሻ እንኳ አይመታበትም። መዶሻውን አስቀምጦ ወደ ሶላት ያመራል። ይህ የኹሹዕ ፊቅህ (ከፍተኛ የግንዛቤ ደረጃ) ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው ለአዛን ጥሪ በፍጥነት ተግባራዊ ምላሽ ሲሰጥ ሶላት ውስጥ ከገባ በኋላ ሀሳቡን ሊቆጣጠር የሚችልን ማንኛውንም ነገር ከራሱ

---

[1] ሓኪምና ጦበራኒ

እየገታ ነው:: ከሶላቱ ውጭ የሚያሳስበው ነገር ስለማይኖር ልቡ በጌታው ፍርሃት ተሞልቶ መስገድ ይቻለዋል:: በአንፃሩ ሥራውን ከቀጠለና ለአዛን ጥሪ ፈጣን ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ ወደ ሶላት በሚገባበት ጊዜ ከነበረበት ሀሳብ የተወሰነውን ይዞ ይሆናል:: እናም ሶላት ውስጥ ሆኖም ሀሳቡን ይቀጥላል፣ ውጤቱም ሶላቱን ማበላሸት ይሆናል:: ለዚህ ነበር አቡ አድደርዳእ (ረ.ዐ.) ተሞክሮአቸውን መሠረት አድርገው ይህንን ምክራቸውን ያስተላለፉት:- "አዋቂ የሆነ ሰው ሶላት ውስጥ ከመግባቱ በፊት ጉዳዩን ሁሉ ይቋጫል:: በዚህም ሶላት ውስጥ ከገባ በኋላ ልቡ ከየትኛውም የዱንያ ሀሳብ የራቀ ይሆናል::"

ኹሹዕን ማሟላት መቻል አዋቂነት ነው፤ አዋቂነት ማለት ደግሞ የመረጃ ብዛት አይደለም፤ አዋቂነት ማለት የአላህን ፍራቻ በቀልብ ማኖር መቻል ነው::

ይህንን ምሳሌ እንመልከት:- አንድ አገልጋይ ወደ አሳዳሪው መጣና "የፈረሱ ኮርቻ ጠፋ" ይለዋል:: አሳዳሪው ፈጠን ብሎ ለሶላት ቆመ:: ከሶላቱ ሲጨርስ ወደ አገልጋዩ ዞወር አለና "ኮርቻውን እዚህ እዚህ ቦታ ታገኘዋለህ" ይለዋል:: አገልጋዩም በሁኔታው በመገረም ለአሳዳሪው እንዲህ አለው:- "ጌታዬ እባክዎን ሶላትዎን በድጋሜ ይስገዱ፤ ምክንያቱም ሶላት ሲሰግዱ ሳይሆን ኮርቻ ሲፈልጉ ነበር የቆዩት::"

## 2. ከስግደት በፊት መስገጃ

አነስ (ረ.ዐ.) እንዲህ ይላሉ:- "ዓኢሻ (ረ.ዐ) ከሱፍ የተሰራ ባለ ብዙ ቀለም መጋረጃ ነበራት:: የቤቷን የተወሰነ ክፍል ትጋርድበት ነበር::" ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሏት:-

"أميطي عنا قرامك هذا فإنه لا تزال تصاويره تعرض لي في صلاتي" (البخاري وأحمد)

‹ይህን ጨርቅሽን አንሽልኝ:: ሶላት ውስጥ ባለሁበት ምስሎቹ ይታዩኛል::›[1]

---

[1] ቡኻሪና አህመድ

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሰዎች መተላለፊያ ቦታ፣ ሁካታ በሚበዛበት ቦታ፣ ወሬ ከሚያወሩ ሰዎች ጎን፣ ቀልድና ጨዋታ ቦታ ላይ ከመስገድ መታቀብ ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይ የዐይንን ትኩረት ከሚስብ አካባቢ መራቅ ይገባል፡፡

## 3. *ከሶላት በፊት አጠናቅቅ*

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

((لا صلاة بحضرة الطعام، ولا هو يدافعه الأخبثان)) *(مسلم وابوداود)*

“ምግብ ቀርቦ ሶላት የለም፤ ሁለት ቆሻሻዎችን እየተጋፋም እንደዚሁ፡፡”[1]

ሁለቱ ቆሻሻዎች የተባሉት ሽንትና አይነ-ምድር ናቸው፡፡ እነኝህን ነገሮች እየታገሉ ኹሹዕ ሊገኝ አይችልም፡፡ ምግብን በተመለከተም ሶላት በሚሰግድ ሰው ፊት ከቀረበ ልቡ ወደ ምግቡ ይንጠለጠላል፡፡ ስለሆነም የራበው ሰው ከሶላት በፊት መመገብ ይኖርበታል፡፡ እስኪጠግብ ድረስም ወደ ሶላት መቻኮል አይኖርበትም፡፡ ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ይህንን አስመልክተው እንዲህ ነበር ያሉት፡

((إذا وضع عشاء أحدكم وأقيمت الصلاة فابدؤو بالعشاء ولا يعجل حتى يفرغ منه)) (البخاري ومسلم واحمد)

“እራት በቀረበበት ሰዓት ለሶላት ኢቃም ቢደረግ ቅድሚያ እራታችሁን ተመገቡ፤ እስከምትጠግቡም ድረስ (ወደ ሶላት) አትቻኮሉ፡፡”[2]

## *እጅግ ውሸታም የሆኑ ሰዎችን ተክቢራ አስጠነቅቅሃለሁ!*

ተክቢረተል ኢሕራም (የሶላት መግቢያ ተክቢራ) የነገስታት ሁሉ ንጉስ ወደሆነው (ጌታ) መግቢያ በር ናት፡፡ ፍጡራን ለፈጣሪያቸው ድህነታቸውን የሚያሳዩበት አስረጂ ናት፤ የጌታን ታላቅነትና የባሪያን ትንሽነት የምትገልፅ የምስክርነት ቃል ናት፡፡

---

[1] *ሙስሊምና አቡ ዳዉድ*
[2] *ቡኻሪ፣ ሙስሊምና አህመድ*



CamScanner

**አሏሁ አክበር** . . . አላህ ከሁሉም ነገር በላይ ታላቅ ነው! ማለት ነው:: እናም በዚህን ጊዜ ዱንያ አንሳ፣ አንሳ ወደ ትክክለኛ ማንነቷ ትመለሳለች:: አላህ ዘንድ የተናቀች እንደመሆኗ አንተም ዘንድ ክብር አይኖራትም:: አላህ ዘንድ የትንኝ ክንፍ ያክል እንኳ ዋጋ የላትምና:: ከእያንዳንዱ ተክቢራ ጋር ይህንን እውነታ በልብህ አኑር:: በመጀመሪያ መቆምህ ላይ ከተዘናጋህ ወደ ሩኩዕ ስታመራ "አሏሁ አክበር!" የሚለው ድምፅ ያነቃሃል፤ ከራስህ ጋር እውነተኛ መሆን የግድ መሆኑን ያስታውስሃል፤ ልብህ ከምላስህ ጋር መጣጣም እንዳለበት ያሳስብሃል:: ሱጁድ ላይ ዘንግተህ ከሆነ ከሱጁድ ስትነሳ "አሏሁ አክበር!" የሚለው ድምፅ ከገባህበት የመዘናጋት ዓለም ያወጣሃል:: ከምላስህ የተነሳው አላህን የማላቅ ቅላጼ ወደ ጆሮህ ይደርሳል፤ ከጆሮህም ወደ ቀልብህ ያመራል፤ እናም የምላስህን ማላቅ ተከትሎ ልብህም ጌታውን ያልቃል::

የሰው ልጅ አስገራሚ ፍጡር ነው… ቀኑን በአላህ ላይ በመዋሸት ሲጀምር ትንሽ አያፍርምን? ወደ ፈጅር ሶላት "አሏሁ አክበር!" ብሎ ሲገባ፣ ከዚያም የመክፈቻ ዱዓኡን፡-

((وجهت وجهي للذى فطر السموات والأرض))

"ሰማያትና ምድርን ለፈጠረ ጌታ ፊቴን አዞርኩ::"

ብሎ ሲያነበንብ የውሸቱን ነበር ማለት ነው:: ስለሆነም ቀኑን በሙሉ ፊቱን የሚያዞረው ለሐራም ስሜቱ፣ ለዱንያዊ ቂብላው፣ ለመዘናጋት መርከቡ፣ ለደመነፍሳዊ አምልኮቱ ይሆናል:: ወንድሜ ሆይ! ኹሹዕን የምትሻ ከሆነ ሶላትህን በእውነት ጀምር፤ የውሸታሞችን ተክቢራ አስወግድ፤ በሸይጧን ፊት የምርህን ጩህበት፤ የተክቢራ ድምፅህን ከልብህ አስተጋባበት "አሏሁ አክበር!!"

### 4. የተሰናባች ሶላት ስገድ

ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ለአባ አዩብ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አደራ ብለውታል፡-

"إذا قمت فى صلاتك فصل صلاة مودع" (احمد وابن ماجه)

“ለሶላትህ ስትቆም የተሰናባች ሶላት ስገድ።”[1]

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለአባ አዩብና ከርሱ በኋላ ለሚመጡት ሁሉ ማስተላለፍ የፈለጉት መልእክት ይህን ይመስላል፡- የሞት ጥላ አጥልሎህ ወደ ሶላት ግባ፤ የሞት መላኢካ ትንፋሽ ለትንፋሽህ ቀርቦ ይሰማህ፤ ልክ ሶላትህን እንዳጠናቀቅክ ተሸቀዳድሞ ሩሕህን እንደሚያወጣት አስብ። ይህች የመጨረሻ ሶላትህ ነች፤ ከዚህች ዓለም መሰናበቻህ ነች፤ የሥራ መዝገብህ የሚጠቀለልበትና ተቆጣጣሪ መላኢኮችህ ሥራ የሚያጠናቅቁበት ጊዜ እንደደረሰ ይሰማህ። ስለሆነም በርሱና ከጌታው ፊት በመቅረብ መካከል ከሶላት ማጠናቀቅ ብቻ የቀረው ባሪያ ዓይነት ሶላት ስገድ። . . . ያኔ የአላህ ፍራቻ ልብህን ይሞላዋል።

ጉዳዩ እጅግ አሳሳቢ በመሆኑ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ደጋግመው አደራ ብለዋል። የአሁኑ አደራ ግን ለአነስ (ረ.ዐ) ሲሆን እንዲህ ነበር ያሉት፡-

((اذكر الموت فى صلاتك، فإن الرجل، إذا ذكر الموت فى صلاته لحري أن يحسن صلاته)) (الديلمى)

“ሶላትህ ውስጥ ሞትን አስታውስ። አንድ ሰው ሶላት ውስጥ ሆኖ ሞትን የሚያስታውስ ከሆነ ሶላቱ ማማሯ የማይቀር ነው።”[2]

አቢ ሐላል አልዐተኪ የዱንያን ቁጥቋጦ ከልባቸው ውስጥ ነቃቅለው ለመጣል የሚጠቀሙበት አስገራሚ መንገድ ነበራቸው። ይህም ሶላት ውስጥ ከመግባታቸው በፊት የሚፈፀም ይሆናል። በተነቀለው ቁጥቋጦ ምትክም የአኼራን ዛፎች ይተክሉበታል። ያ ዛፍ ሲወዛወዝ አላህን የመፍራት ፍሬ ይረግፋል። አቢ ሐላል ግን ቸር ሰው ነበሩ። ትሩፋቱን ከሌላው ሰው አልደበቁም። አስተዋይ በመሆናቸው በአንድ መልካም ስራ በርካታ ምንዳ ማግኘት እንደሚችሉ ያውቃሉ። ታዲያ ምን ያደርጉ ነበር መሰላችሁ። የክፍላቸውን የተወሰነ በር ይከፍቱና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው፡- “አንተ እገሌ የእገሌ ልጅ ሆይ!” ብለው ይጣራሉ። የሚጣሩት ከሞቱ ሰዎች መካከል አንዱን ነው። በሌላኛውም አቅጣጫ እንደዚሁ

---

አህመድና ኢብኑ ማጃህ
ኣድ-ደይለሚይ

ይጣራሉ:: በአራቱም አቅጣጫ የሞቱ ሰዎችን ስም ከፍ ባለ ድምፅ ከተጣሩ በኋላ ሱረት መርየም ውስጥ የሚገኘውን አንቀጽ ያነባሉ:-

﴿...هَلْ تُحِسُّ مِنْهُم مِّنْ أَحَدٍ أَوْ تَسْمَعُ لَهُمْ رِكْزًا ﴾ مريم: ٩٨

"...ከነርሱ ውስጥ አንድን እንኳ ታያለህን? ወይስ ለነሱ ሹክሹክታን ታሰማለህን?" (መርየም: 98)

ይህንን አንቀጽ አንብበው የሞት ትውስታ በእርሳቸውም ሆነ በሰሚቸው ሰዎች ልብ ውስጥ ይሰፍንና ወደ ሶላት ይገባሉ:: በዚህ ዓይነት ስሜት ውስጥ ሆነው የሚሰግዷት ሶላት ምንኛ ታምር!

## 5. ቁርአንን በተስተካከለና በሚያምር ድምፅ አንብብ

ቁርአን በዝግታ ማንበብ አላህ (ሱ.ወ) ነቢያችንን (ሰ.ዐ.ወ) ያዘዘበት ጉዳይ ነው:-

﴿...وَرَتِّلِ ٱلْقُرْءَانَ تَرْتِيلًا ﴾ المزمل: ٤

"ቁርኣንንም በዝግታ ማንበብን አንብብ::" (አል-ሙዘሚል: 4)

ለዚህ ነበር የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የቁርአን አነባበብ ፊደል በፊደል የተበተነ የነበረው:: ይህ ዓይነቱ ረጋ ያለ አነባበብ ለማስተንተንና የአላህን ፍራቻ ወደ ልቦና ለማምጣት ጠቃሚ ነው:: በፍጥነትና በችኮላ ማንበብ ይህንን ውጤት አያስገኝምና:: ከዝግታው በተጨማሪም ድምፅን ማስዋብ ድንቅ የሆነ የረሱላችን (ሰ.ዐ.ወ) የአደራ ገፀ-በረከት ነው:: እንዲህ ይላሉ:-

((زينوا القرآن بأصواتكم، فإن الصوت الحسن يزيد القرآن حسنا)) (الحاكم)

“ቁርአንን በድምፃችሁ አስውቡት፤ ማራኪ ድምፅ ለቁርአን ውበትን ይጨምርለታልና::”[1]

ድምፁ ማራኪ ያልሆነ ሰው ደግሞ ሊሸማቀቅ አይገባም:: ምክንያቱም ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) በሌላ ሐዲሥ ላይ የድምፅ ውበቱ የሚለካው አንባቢው ለአላህ ባለው ፍራቻ (ኹሹዕ) መሆኑን እንዲህ ሲሉ ይገልፃሉ፡-

" أحسن الناس قراءة الذى إذا قرأ رأيت أنه يخشى الله " *(البيهقى)*

“ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ የሚያምር የቁርአን አንባቢ፡- በንባቡ ጊዜ የአላህ ፍራቻ የምታነበበት ነው::”[2]

## 6. ቁርአንን አስተንትን፤ ተመሰጥም

ወደ “ኹሹዕ” የብስ መድረስ የፈለገ በ “ተደቡር” (ማስተንተን) ባህር ውስጥ መዋኘት ይኖርበታል:: በእንባ ወንዝ ውስጥ መስጠም ይጠበቅበታል:: የተላቀው ጌታህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ كِتَٰبٌ أَنزَلْنَٰهُ إِلَيْكَ مُبَٰرَكٌ لِّيَدَّبَّرُوٓا۟ ءَايَٰتِهِۦ وَلِيَتَذَكَّرَ أُو۟لُوا۟ ٱلْأَلْبَٰبِ ﴾ ص: ٢٩

“(ይህ) ወዳንተ ያወረድነው ብሩክ መጽሐፍ ነው:: አንቀጾቹን እንዲያስተነትኑና የአእምሮዎች ባለቤቶችም እንዲገሰጹ (አወረድነው)::” *(ሷድ፡ 29)*

ከልቡ በመመሰጥ ቁርአንን ያስተነተነ ሰው ዐይኑ ታለቅሳለች:: ቁርአን ከጉሮሮው አልፎ ቀልቡ መድረስ ያልቻለ ሰው ልቡ ይደርቃል፤ የዐይኑ እንባ ይነጥፋል:: የቁርአን ተርጓሚው ሊቅ ዐብደላህ ኢብን ዐባስ (ረ.ዐ.) እንዲህ ይላሉ፡- “ሱረቱ አል ኢስራእ የሚገኘው ሰጅደህ (ሱጁድ የሚደረግበት አንቀጽ) ላይ ስትደርሱ ሱጁድ ለማድረግ አትቸኩሉ:: በቅድሚያ አንቀጹን አስተንትናችሁ አልቅሱ:: ዐይናችሁ ባያለቅስ እንኳ ልባችሁ ያልቅስ::”

---

[1] *አል-ሓኪም*
[2] *አል-በይሀቂ*

ሱረቱ አል-ኢስራእ ላይ የሚገኘው አንቀጽ እንዲህ ይነበባል፡-

﴿قُلْ ءَامِنُوا۟ بِهِۦٓ أَوْ لَا تُؤْمِنُوٓا۟ ۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْعِلْمَ مِن قَبْلِهِۦٓ إِذَا يُتْلَىٰ عَلَيْهِمْ يَخِرُّونَ لِلْأَذْقَانِ سُجَّدًا ﴿١٠٧﴾ وَيَقُولُونَ سُبْحَٰنَ رَبِّنَآ إِن كَانَ وَعْدُ رَبِّنَا لَمَفْعُولًا ﴿١٠٨﴾ وَيَخِرُّونَ لِلْأَذْقَانِ يَبْكُونَ وَيَزِيدُهُمْ خُشُوعًا ۩ ﴿١٠٩﴾﴾

"…እነዚያ ከእርሱ በፊት ዕውቀትን የተሰጡት በእነሱ ላይ በተነበበ ጊዜ ሰጋጆች ኾነው በሸንጎበቶቻቸው ላይ ይወድቃሉ፤ ይላሉም ጌታችን ጥራት ይገባው! እነሆ የጌታችን ተስፋ ተፈጻሚ ነው:: እያለቀሱም በሸንጎበቶቻቸው ላይ ይወድቃሉ (አላህን) መፍራትንም ይጨምርላቸዋል::[۩]" *(አል-ኢስራእ- 107-109)*

የልብ ለቅሶ በጥሞና ማስተንተን ነው፤ ያ ማስተንተን ደግሞ አላህን መፍራት ይፈጥራል:: የልብ ለቅሶ የዐይን ለቅሶን ማስከተሉ አይቀሬ ነው:: እናም ይህን ስሜት ካየህ የሚፈለገው መጨረሻ ላይ መዳረስህን አበስርሃለሁ:: በጥልቀት ለማስተንተን ከሚጠቅሙ መንገዶች መካከል ዋንኛው አንቀጾችን ደጋግሞ ማንበብ ነው:: ይህንኑ ነበር ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያደርጉ የነበረው:: ከዕለታት በአንዷ ሌሊት አንድ አንቀጽ ብቻ እየደጋገሙ እስከንጋት ድረስ ቆመዋል:: አንቀጹዋም ይህች ነች፡-

﴿إِن تُعَذِّبْهُمْ فَإِنَّهُمْ عِبَادُكَ ۖ وَإِن تَغْفِرْ لَهُمْ فَإِنَّكَ أَنتَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ﴾ المائدة: ١١٨

«ብትቀጣቸው እነርሱ ባሮችህ ናቸው::ለነርሱ ብትምርም አንተ አሸናፊው ጥበበኛው ነህ» (ይላል):: *(አል-ማኢዳህ፡118)"*

## 7. *የሶላትን መልዕክት በጥልቀት ተረዳ*

የሶላት ሁሉም ሥነ-ሥርዓቶች የሚያስተላልፉት መልዕክትና የራሳቸው ትርጉም አላቸው::

***ዉዱእ*** . . . ሰማይ ንጹሕ ውሃን በአንተ ላይ በማዝነብ በአንተ የንጽሕና ሂደት ላይ አስተዋፅኦ ታደርጋለች:: ይህ ንጽሕናህ የከፍታህ፣ የልዕልናህና የምጥቀትህ መነሻ ነው:: በዚህ ንፅህና የክፉ ስሜት አቧራን ታጥባለህ:: እጅህን፣ እግርህንና መላ አካላትህን ያለበሰውን ቆሻሻ